የወ/መ/ቁጥር 155074

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ ወ/ሮ ወርቂቱ በዳኔ - ከጠበቃ ሀብታሙ ጋር ቀረቡ

2 ኛ አቶ ግርማ ፀጋዬ ተድላ - ከጠበቃ ሀብታሙ ጋር ቀረቡ

3 ኛ ወ/ሪት መነን ፀጋዬ ተድላ - ተወሰነ

መዝገቡ ተመርምሮ በ 1 ኛ እና 2 ኛ ተከሳሾች ላይ የሚከተለው ቅጣት ተወሰነ

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

አንደኛ ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለችበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 585(1) እና 2 ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 585(2)(ሀ)/ ሌላ ሰውን ከሕግ ውጭ ይዞ ማስቀመጥ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ

የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን አፈፃፀም ሲመረምረው አንደኛ ተከሳሽ የግል ተበዳይን ሁለተኛ ተከሳሽ ከሌሎች ሰዎች ጋር ይዞ ሲያመጣ በመቀበል በቤታቸው ውስጥ እንዲቀመጡ ያደረጉ ብቻ በመሆኑና ይህ ደግሞ የአፈፃፀሙን ከባድነት የሚያመለክት ባለመሆኑ አንደኛ ተከሳሽን በተመለከተ የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ነው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን፤ ሁለተኛ ተከሳሽን በተመለከተ ግን የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ ሲታይ የግል ተበዳይን ለቀጠሮ ከቆሙበት ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን አፍኖና በኃይል ይዞ ወደ ቤት ወስዶ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የግል ተበዳይን አስሮ ያስቀመጠ ስለሆነ የወንጀል ደረጃው ከባድ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 585(1) ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከሦስት ወር ቀላል እስራት እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት ሲሆን፤ በሕጉ አንቀፅ 585(2)(ሀ) ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ነው። በዚህም መሰረት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት አንደኛ ተከሳሽን በተመለከተ ዝቀተኛ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከሦስት ወር እስከ ስምንት ወር ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት አምስት ወር ቀላል እስራት መነሻ ቅጣት ተብሎ ሲወሰን፤ ሁለተኛ ተከሳሽን በተመለከተ ከባድ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከሦስት ዓመት እስከ አራት ዓመት ባለው መካከል ውስጥ ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት ሦስት ዓመት ከአራት ወር መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት የአንደኛ ተከሳሽ በአባሪ 1 እርከን 3 ላይ የሚታይ ሲሆን፤ የሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ በአባሪ 1 እርከን 16 ላይ የሚታይ ይሆናል።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት የቅጣት ማክበጃ ምክንያት በማለት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሀ)፤ (መ) እና (ሠ) ላይ የተጠቀሱትን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ሲመረምራቸውም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሀ) ላይ የተገለፀውን በተመለከተ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ላይ በሚያሚላ መልኩ ያልቀረበ ስለሆነ ይህን ነጥብ ፍ/ቤቱ በማክበጃነት አልወሰደውም። በሌላ በኩል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(መ) እና (ሠ) ላይ የተገለፁትን በተመለከተ ድርጊቱ በጋራ የተፈፀመ በመሆኑና ተከሳሾች ይህን ድርጊት የፈፀሙት የአንደኛ ተከሳሽ ባለቤት የነበሩ፤ ለሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ አባት በሆኑት ላይ የተፈፀመ ስለሆነ ሁለት የቅጣት ማክበጃዎችን ፍ/ቤቱ በመውሰድ አንደኛ ተከሳሽን በተመለከተ እርከኑ ወደ 5 ከፍ ሲል፤ ሁለተኛ ተከሳሽን በተመለከተ ደግሞ ወደ እርከን 18 ከፍ ይላል።

በሌላ በኩል ተከሳሾች የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82(1)(ሀ) ላይ በተመለከተው መሰረት ከአሁን በፊት በሌላ የወንጀል ድርጊት ስለማይታወቁ ቅጣቱ ይቅለል በማለት የተከሳሾች ጠበቃ ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሾች የአሁኑን የወንጀል ድርጊት እስከፈፀሙበት ጊዜ ድረስ በመልካም ሁኔታ መኖራቸው ብቻውን እንደ ቅጣት ማቅለያ ሆኖ በሕጉ ላይ ያልተመለከተ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የማቅለያ ምክንያቱን አልተቀበለውም። ሌሎች የቅጣት ማቅለያ ተብለው የቀረቡት ደግሞ በማስረጃ የተደገፉ ባለመሆኑና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት ደግሞ ፍ/ቤቱ ልዩ ማቅለያ ምክንያት ያላገኘ ስለሆነ እንዲሁም ተከሳሾች ያቀረቡት የቅጣት አስተያየቶች ፍ/ቤቱ በፍቅድ ስልጣኑ ውስጥ ለመንሸራሸር የሚረዱ እንጅ የቅጣት ማቅለያዎች ባለመሆናቸው ፍ/ቤቱ የመነሻ ቅጣት እርከኑን ዝቅ አላደረገውም። በመሆኑም ከላይ በማክበጃ ምክንያት ከፍ ያለው የቅጣት እርከንን ፍ/ቤቱ እንዳሉ ወስዷቸዋል።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ ከላይ በተመለከቱት እርከኖች መሰረት አንደኛ ተከሳሽ በእርከን 5 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ስለሆነ ተከሳሽን ያርማቸዋል፤ ወደፊትም ያስተምራቸዋል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በሰባት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል። ሁለተኛ ተከሳሽን በመለከተ ደግሞ የእርከን 18 ፍቅድ ስልጣን ከሦስት ዓመት ከሰባት ወር እስከ አራት ዓመት ከአራት ወር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹን ለፈፀመው ጥፋት ያርማል፤ወደፊትም ያስተምረዋል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በአራት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ተከሳሾች እጃቸው ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በማሰብ
የተወሰነውን የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል። ተከሳሾች ከዚህ ቀደም
በዚሁ ጉዳይ በፖሊስ ጣበያ ለአርባ ሰባት/47/ ቀናት ያህል የታሰሩ ስለሆነ
ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ እንዲያስፈፅም ማ/ቤቱ ታዟል። በተጨማሪያም
ሁለተኛ ተከሳሽ አቶ ግርማ ፀጋዬ በሽተኛ በመሆኑ የአዲስ አበባ ማረሚያ
ቤት ተከሳሹ ተገቢውን የህክምና ክትትል እንዲደረግለት እንዲያደርግ
እንዲሁም ተከሳሹ በአለርት ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚ ስለሆነ የማረሚያ
ቤቱ ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት ሐኪም በቀጠረው መሰረት
ህክምናውን እንዲከታተል እንዲያደርግ ማ/ቤቱ እንዲያስፈፅም ታዟል።
ይፃፍ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. ይህ የቅጣት ውሳኔ ዛሬ ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ተነበበ።

4 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

5 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝጉብ ቤት ይመለስ።